በኑ ኢስራኢሎችን ነቢያቶች ነበሩ ጉዳያቸውን የሚመሩት። አንድ ነቢይ በሞተ ቁጥር ሌላ ነቢይ ይተካ ነበር። ከኔ በኋላም ነቢይ የለም። ምትኮች (ኸሊፋዎች) ይኖራሉም ይበዛሉም።

ከአቡ ሓዚም እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «አቡ ሁረይራ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ዘንድ አምስት ዓመት ተቀምጫለሁ። ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብሎ ሲያወራም ሰምቸዋለሁ: "በኑ ኢስራኢሎችን ነቢያቶች ነበሩ ጉዳያቸውን የሚመሩት። አንድ ነቢይ በሞተ ቁጥር ሌላ ነቢይ ይተካ ነበር። ከኔ በኋላም ነቢይ የለም። ምትኮች (ኸሊፋዎች) ይኖራሉም ይበዛሉም።" ሶሐቦችም "ምን ያዙናል?" አሉ። እርሳቸውም "የመጀመሪያውን ቃል ኪዳን ሙሉ፤ ሐቃቸውንም ተወጡ። አላህም ለሰጣቸው ሀላፊነት ይጠይቃቸዋል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዛሬ ላይ ህዝቦችን የሚመሩት መሪዎችና ሹማምንት እንደሆኑት ያኔ በኒ ኢስራኢሎችን የሚመሯቸውና ጉዳያቸውንም በሀላፊነት የሚያዙት ነቢያቶች እንደነበሩ ተናገሩ። ብክለት በመካከላቸው በተንሰራፋ ቁጥርም ጉዳዩን የሚያስተካክልና የለወጡትን ህግ የሚያስወግድ ሌላን ነቢይ አላህ ይልክ ነበር። በነርሱ ላይ ያደርግ እንደነበረው የሚያደርግ ከኔ በኋላ የሚመጣ ነቢይ የለም። ከኔ በኋላ ምትኮች (ኸሊፋዎች) ነው የሚኖሩት እነርሱም በርካታ ይሆናሉ። በመካከላቸውም ልዩነትና ተቃርኖ ይከሰታል። ሶሐቦችም - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - የአላህን መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) "ምን ያዙናል?" በማለት ጠየቁ። እርሳቸውም "ከአንዱ መሪ በኋላ ለሌላ መሪ ቃል ኪዳን ቢገባለት። የመጀመሪያው መሪ ቃልኪዳን ትክክለኛ ስለሆነ ታማኝ መሆን ያለባችሁ ለመጀመሪያው ነው። አንድ መሪ እያለ ለሁለተኛ መሪነት ቃል የተገባለት ግን ቃልኪዳኑ ተቀባይነት የሌለው ከንቱ ነው። እርሱም መሪነትን መፈለጉ ክልክል ነው። ለመሪዎች ሐቃቸውን ስጧቸው፣ ታዘዟቸው፤ ከወንጀል ውጪ በመታዘዝና በመስማትም ተኗኗሯቸው። በናንተ ላይ ለሚሰሩት ነገር አላህ ይጠይቃቸዋልም ይታሳሰባቸዋልም።"

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4936